# እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል

ከኃይለ ልዑል ግርማ
ዋሽንግተን ዲሲ

የወያኔ አምባገነን አገዛዝ በአስራ አራት ዓመቱ በሕዝብ ውሳኔና ምርጫ ያበቃለትና ያከተመለት መሆኑ ከታወቀ በኂላ በውስጥና በውጭ ጠላቶቻችን ቅንብር አስከፊ የሆነ ጨካኝ ጭፍጨፋና እርምጃ በመውሰድ የሕዝብን ጽምጽ በመሳሪያ ኃይል በማፈንና በመንጠቅ የስልጣን እድሜውን ሲያራዝም፤ የወያኔ ከፍተኛ ባለሥልጣኖችና የነፍስ አባቶቹ የሞተውን ወያኔ ነፍስ ዘርተውበት የሕዝቡን ትግል ለማዳፈን ሞክረዋል::

በታሪክ ተሰምቶና ታይቶ የማይታወቅ አሸናፊ ወደ እስር ቤት ተሸናፊ ቤተመንግሥት የቀዩበት ጊዜና ቦታ ቢኖር የእኛ አገር ውስጥ ብቻ ነው ማለት ይቻላል:: የቅንጅት የፓርላማ ተመራጮች በአንድ አምባገነንና ዘረኛ ቡድን መሪ የፓርላማ ተመራጭነት መብታቸው ተገፎ ወህኒ ሲጣሉ፣ በሀገር ክህደት ሲከሰሱ፣ በገዳይና በአስገዳይ ምትክ ሲወነጀሉ ድፍን ዓለም ሰምቶ ዝም ብሏል:: ምክንያቱም የኢትዮጵያ ጠላቶች በሙሉ የኢትዮጵያን ሉዐላዊነት የሚያስጠብቅ፣ ለሕዝቡ የሚቆረቆር፣ በአገሩ ጉዳይ የማይደራደር ጀግና ኢትዮጵያዊ አይፈለግምና ወያኔን በመደገፍና በማቆየት ኢትዮጵያን የማፈራረስ እቅዳቸውን በተቀነባበረ መንገድ ለመቀጠል ነው::

የቅንጅት መሪዎች ከታሰሩ በኋላ እስር ቤት ውስጥ በተካሄደ ከፍተኛ ሴራ የወያኔን እድሜ ለማራዘም በጥቅምና በፍርሃት ለሆዳቸው ባደሩ ከሃዲዎች አማካኝነት የትግሉን አቅጣጫ ለማስቀየር የተሞከረው ደባ ለተወሰኑ ጊዜያት በአገርም ሆነ በውጭው ዓለም በደጋፊዎች ዘንድ ከፍተኛ ግራ መጋባት፣ ተስፋ መቁረጥና መከፋፈልን ሊፈጥር ችሏል:: እውነትና ሀሰቱን ለመለየት በሚያዳግት ደረጃ የተቀነባበረ ሴራ ተሰርቶ ትግሉን ለማዳፈን ተሞክሯል:: በገንዘብ የተገዙ ቅጥረኞች በአገር ወዳዱ ክፍል ላይ ከፍተኛ የስም ማጥፋት ዘመቻ በማካሄድ ደጋፊውን ክፍል በየቤቱ እንዲከተት፣ እርስ በእርሱ እንዲሻኮት፣ እንዲከፋፈልና እንዲለያይ አድርገዋል:: በብዙ ጽሑፎችና ስብሰባዎች ላይ እንደተገለጸው የዚህ አደገኛ ከፋፋይ ስራ መሃንዲሶቹ እነ አንዳርጋቸው ጽጌ፣ ብርሃነ መዋ፣ ዶ/ር ሞገስ ገብረማርያም፣ ደቀመዝሙሮቻቸው ግርማ ካሣ፣ ፈቃደ ሸዋቀና፣ ይልማ አዳሙ፣ አሸብር ወዘተ... እና በአውሮፓና እና አጠገባችንም የካናዳ ካድሬዎቻቸው አማካኝነት ይህ ነው የማይባል ወንጀል ፈጽመዋል:: ትግሉን ለማዳፈን በረቀቀ ስልት ከመጀመሪያውኑ የተነሱት መሪዎቻቸው ደግሞ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ፣ እርሱ የፈጠራት አሻንጉሊቱ ብርቱካን ሚዴቅሳ፣ ከሃዲው ኢንጂነር ግዛቸው ሺፈራው እና ሌሎች ጥቂት አፈንጋጮች በቅንጅት ስም ከተራወጡና የውጭ ነዋሪውን ኪስ ካራቆቱ በኋላ የኢትዮጵያን ሕዝብ ማታለል የሚችሉ መስሏቸው ወዲያ ወዲህ ይላሉ:: ዋናው ዓላማቸው በሕዝብ ትግል ላይ ቀዝቃዛ ውሃ አፍሰው፣ ትግሉን ለወያኔ ሸጠው፣ እንደነ በየነ ጴጥሮስ ታማኝ ተቃዋሚ መስለው ለመኖር ነው:: ለምርጫ 2010ም የወያኔ ድራማ ተዋናኝ ሆነው ለመቅረብ በጥቅምና በሆዳቸው ተገዝተው ነው:: **የብዙ ኢትዮጵያኖች ሕይወት የተሰዋበት፣ ደም የፈሰሰበት፣ የታሰረበት፣ ቤተሰቡንና ንብረቱን ያጣበት፣ የተሰቃየበት፣ የተሰደደበት ትግል በጥቂት ሆዳምና ከሃዲ ግለሰቦች አማካኝነት** መና ሊቀር ከቶም አይታሰብም:: የኢትዮጵያችን የወደፊት እጣ በሕዝቡዋ እንጂ በኢትዮጵያ ጠላቶች እጅ መሆን የለበትም:: እውነቱ መታወቅና መነገር አለበት:: ወዲያ ወዲህ የለም:: የተጀመረው የነጻነትና የዲሞክራሲ ትግል መቀጠል አለበት:: መስዋዕትነት ተከፍሏል ወደፊትም ያስከፍላል:: ለክቡር ዓላማ ክቡር መስዋዕትነት መክፍል ኢትየጵያዊነት በመሆኑና ለዚህም የቆሙ ቆራጥ መሪዎችና ጀግኖች ታጋዮች ስላሉ ድሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደሚሆን ምንም ጥርጥር የለውም::

ዛሬ ጎራው ለይቶ የሕዝብ ወገን እና የጠላት ወገን አለ:: ከኢትዮጵያ የአንድነት ኃይል ወገን ካልሆነ አንድ ሰው ከጠላት ወገን መሆኑ ነው:: የምናወራው ስለ አንድ ፓርቲ ወይም ቅንጀት ፓርቲብቻ አይደለም:: ስለ ኢትዮጵያ መኖርና አለመኖር ነው:: ስለሕዝቧ ነጻነትና ባርነት ነው:: ስለታሪኳ ከዓለም ገጽ መፋቅና ለትውልድ ማስተላለፍ ነው:: ስለ ሕዝቧ በጎሳ መከፋፈልና በአንድነት መኖር ነው:: በወያኔ ኢትዮጵያ ትኖራለች የሚል

ወይ ጨርሶ ኢትዮጵያዊነት ምን እንደሆን የማያውቅ አሊያም በኢትዮጵያዊነት ስም ኢትዮጵያን ለማጥፋት የሚቆም ከሃዲ ብቻ ነው። ወያኔ የኢትዮጵያ ጠላት ከሆነ ማንም ይሁን ማን የትም ይሁን የት የሚደግፈው ሁሉ ከጠላት ጋር አበረ ማለት ነው። ወያኔን የሚደግፍ ሁሉ የግል ጥቅሙን የሚያስቀድም ከሃዲ፣ ሆዳም፣ አድርባይ፣ የተገዛ ጥቅመኛ ወይም የኢትዮጵያ ጠላት ነው። እስከዛሬም እንዲህ ተብሎ ጎራው ስላልለየ ነው የዘመኑ ሆዳም ለጥቂት ካሪ ሜትር ቦታ ለማግኘትና ንግድ ቤት ፈቃድ ለማግኘት ሲል ከጠላት ጋር በማበር የሕዝብ ትግልን ለመግደል የወያኔ ተባባሪ እየሆነ ያለው።

ቅንጅትን በተመለከተ ትክክለኛው መስመርና የትግል ጎዳና በኢንጂነር ኃይሉ ሻውል የሚመራው ቅንጅት ብቻ ነው። ሌላው በውጭ መንግሥት አማካኝነት የተቀመጡ ግለሰቦች የታዘዙትን የሚያደርጉ የወገን ጠላት ክፍል ነው። አንዳንዱም በኃይለሥላሴም በደርግም ዛሬም በወያኔ ጊዜ በአድርባይነት የሚሰራው ምሁር ተብዬው ከሃዲ ክፍል ነው። በስተእርጅና እድሜያቸው ከነብርቱካን ጋር ዘጥ ዘጥ የሚሉት ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም እጅግ በሚያሳፍር ጎዳና ላይ መውደቃቸው ካለማወቅ ሳይሆን ለረጂም ዘመናት ተቀብሮ የቆየ ቀጣይ ስራ ነው። እነ ክፍሉ ታደሰ፣ ያሬድ ጥበቡ  ወዘተ ለማን እንደሚሰሩ የታወቀ ነው። የኢሕአፓ ባለፈው ዓመት የተገነጠሉት አንጃዎች ሰላሳ አምስት ዓመት በትግሉ ቆይተው ዛሬ በሚያሳፍር ጎዳና ላይ መጓዛቸው የትግሉ ውጤት ስለዘገየባቸው የሥልጣን ፍርፋሪ ከወያኔ ቢወድቅልን ብለው ከማሰብ የተነሳ ነው። ዓላማቸው ሥልጣን ከሆነ ኢትዮጵያን ረስተዋልና እጣ ፈንታቸው ከነብርሃኑ ነጋ ጋር ነው። እውነቱን አውቀውና ተረድተው ከተመለሱ እሰየው ከሄዱም የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍርድ ይጠብቃቸዋል።

በኪነት ክፍል ዝነኛና ታዋቂ የነበሩት በጥቅም ተገዝተው "መቻቻል"፣ "እርቅ"፣ "ልማት" ወዘተ... እያሉ የኢትዮጵያን ሕዝብ ፍቅር በገንዘብና በጥቅም ለውጠው ለወያኔ በመስራት ላይ ናቸው። አሜሪካ ዋሽንግተን ዲሲ በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን ኔትወርክ ስም የተሰባሰቡ አርቲስቶች ሁሉ በዚያው ጎራ መግባታቸውን ሕዝብ ሊያውቅ ይገባል። በእነ ሰዬ አብርሃ፣ በእነብርሃነ መዋ እና ብርሃኑ ነጋ የሚመራው (ETN)የቴሌቭዥን ጣቢያ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም አይደለም የተቋቋመው። በውጭ ያለውን ነዋሪ ለማዘናጋት እና ቀስ በቀስ የወያኔን የቴሌቪዥን ፕሮግራምን ለማምጣት ነው። በቅርቡም ቴለቪዥን ጣቢያውን ከአዲስ አበባ ጋር ለማገናኘትና የወያኔን ፕሮፓጋንዳ ለማስተላለፍ በመስራት ላይ ያሉት ለምን እንደሆነ ግልጽ ነው። በአሜሪካና በካናዳ በየከተማው እንደአሸን የፈሉት ሬዲዩ ጣቢያዎችና ቴሌቭዥን ፕሮግራሞች የሚካሄዱት በእነማን ነው ብሎ መጠየቅና ማወቅ በጣም ይገባል። ሰሚ ጠፋ እንጂ ከሁለት ዓመት በፊት የወያኔ ሃምሳ ሁለት ገጽ ማንዋል በውጭ ያለውን የዲያስፖራ እንቅስቃሴ ለመግታት ታልሞ በሥራ ላይ እየዋለ መሆኑ የተነገረው ዛሬ ግልጽ ብሎ ይታያል።  ወያኔ በውጭ ያለውን የተቃውሞ እንቅስቃሴ ለማፈን ሚዲያውን መያዝ ዋናው ስራ አድርጎ እየሰራ ነው። ወገኖች በገዛ ገንዘባችን ሰለባ አንሁን። መለየት ያስፈልጋል።  የቀድሞ ዝነኛ አርቲስቶች የዛሬ ታሪካቸውን ብንከታተል ደግሞ አንዱ አንዱን በመጎተት በወያኔ የድጋፍ ፕሮግራም ውስጥ እየገቡ መሆናቸውን እያየን ነው።  የነሆዳሙን ሰለሞን ተካልኝን ሳንረሳ ባለፈው ሳምንት አርቲስት አስቴር አወቀ የሰላሳ ሚሊዮን ብር ፕሮጀክት ለማካሄድ 6000 ካሬ ሜትር ደብረ ዘይት ቦታ ሲሰጣትና ከወያኔ ጋር ስትፈራረም ለኢትዮጵያ ሕዝብ አስባ አይደለም። እነ ታማኝ በየነ ሰላሳ ቦታ እየረገጡ ሲያምታቱ፣ እነአበበ በለው ሲቀላምዱ እነ ዳዊት ከበደ አይን ሲያወጡ እነ ኤልያስ ክፍሌ የትግል መሪ ሲሆኑ አረ በአገራችን ላይ ምን እየተዶለተ ነው ምን እየተሰራ ነው ብሎ መጠየቅ ብልህነት ነው።

ሆዳሙን፣ ከሃዲውን፣ ጥቅመኛውን ደፍረን ለመናገር ባለመቻላችንና እርምጃም ባለመውሰዳችን የጥቅም ማግኘቱ ስራ ቦታው ሳይሞላ ሁሉም ሲራኮት ሆዱን ሲመለከት አገሩን እየጎዳ ነውና ማሳወቅ፣ ማስጠንቀቅና እርምጃ መውሰድ ተገቢና ጊዜውም ነው። ስለሆነም ሕዝብ ፊቱን ሳያዞርባችሁና እንደ ልደቱ አያሌው አይናችሁን ላፈር ሳይላችሁ በፊት ማሰብና መጠንቀቅ አለባችሁ። ማንም ይሁን ማን ኢትዮጵያን ከሚጎዳ ጠላት ጋር ሲሰራ ከተገኘ ከጠላት ጎራ መፈረጁ አይቀሬ ነው። መጠየቁም የማይቀር ነው።

በአገራችን ያሉትን በሱስ የማደንዘዣ ቤቶችና ስፍራዎች ሳያንሱ በውጭ አገር በየከተማው የተከፈቱት የጫት መቃሚያ ቤቶች ምን እንደሚሰሩ ማወቅና መከላከል የሁላችንም ኃላፊነት ሊሆን ይገባል። አንደኛ በስንት ሩጫ የሚኖረውን የውጭ ነዋሪ በጫት፣ በትምባሆና በመጠጥ በማደንዘዝ ኋላ ቀር ከማድረጉም በላይ የጤና ችግርና የኢኮኖሚ ቀውስ የሚያስከትል ጎጂ ድርጊት ወይም ሱስ ነው። ሁለተኛው የወያኔ ደጋፊዎች መርዛቸውን የሚረጩት፣ አሉባልታቸውን የሚያሰራጩትና አዲስ መጤውን "አንተ ሰው ሁሉ ቦታ ሲያገኝ ቤት ሲሰራ በንግድ ሚሊየነር ሲሆን ድሃ ሆነህ ተቀምጠሃል" እየተባለ ከወያኔ ካምፕ የሚያስገቡበት ወጥመድ ነው። ይህንን ሆን ብለው እንደ ሥራ የያዙ የወያኔ ተላላኪዎች በጨዋታ መልክ የወያኔን ፕሮፓጋንዳ የሚነዙና ይህን ህገወጥ የጫት ተግባር እንዲስፋፋ የሚያደርጉትን መከላከልና ማስቆም ይቻላል።

ወጣት ሴት እህቶቻችንን በፋሽንና በስልጣኔ ስም ከባሕላቸው ወጥተው የውጭውን አሳፋሪና ርካሽ ባህል እንዲከተሉ የሚያደርጉም ክፍሎች አሉ። መልካም ባሕልን፣ ቋንቋንና አስተሳሰብን፣ እውቀትና ለአገር ማሰብን እርግፍ አድርገው እንዲተዉ እና በርካሽና አስነዋሪ ባሕልና ቅጥ አምባሩ በጠፋ ጉራማይሌ ቋንቋ እየተጠቀሙ ነውና ብዙ ገፍቶ ከቁጥጥር ውጭ ሳይወጣ በቶሎ እንዲገታ ሊታሰብበት ይገባል። ኢትዮጵያዊ ቋንቋና ባሕል ኋላ ቀርነት አድርገው እንዲመለከቱ መደረጉ ነገ የማንነት ጥያቄ ውስጥ እንዲወድቁና ከኢትዮጵያዊነት እንዲሸሹ መደረጉ አንዱና ከፍተኛ የጥፋት መንገድ ነው።

ሌላው መታወቅ ያለበት በኢንተርኔት የተጻፈ ሁሉ ትክክል ነው ብለው የሚያምኑ ሞኛሞኞች የትኛው የዜናና ትክክለኛ መረጃ ማግኛ ክፍል የሕዝብ፣ የትኛው የወያኔ መሆኑን ለይተው ማወቅ አለባቸው። የወያኔን ፕሮፓጋንዳ የሚነዙ ዌብ ሳይቶች፣ ቴሌቪዥን ፕሮግራምና ሬዲዮ መከታተሉ በቀላሉ ለወያኔ የፕሮፓጋንዳ ሰለባ በገዛ ጊዜና ገንዘብ መጋበዝ ነው። ሕዝብ በረሃብ ሲሰቃይ፣ በድህነት፣ በበሽታ ሲያልቅ አገራችን አደገች እያሉ የሚዋሹበትን ፕሮግራም መከታተሉ ሞኝነትና አደገኛም ነው።

የወያኔ ቅጥረኞች ባለፉት ሁለት ዓመታት ያካሄዱትን የስም ማጥፋት ዘመቻ፣ የመከፋፈል ደባና ሴራ በሚገባ አውቀን "መቻቻል" "መታረቅ" የሚሉ ቃላቶችን በመደርደር ወንጀለኛውን ከሀቀኛውና ከአገር ወዳዱ ሳይለዩ መናገሩ ከጠላት ጋር ተስማምታችሁ አገራችሁን አጥፉ ተባበሩ እንደማለት ነው። ከጠላት ጋር አይሰራም። መሞዳሞድም አያስፈልግም። የኢትዮጵያ ጠላት መወገድ አለበት። ከአንድነት ኃይሉ ጋር መቆም እንጂ ሌላ አማራጭ የለም። ለዚህም ከክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል አመራር ጋር የቅንጅትን ትግል ከግቡ ለማድረስ በቆራጥነት መጓዝ አለብን። እነ ብርቱካን መንገዳቸውን ለይተው ወጥተዋል። በቅንጅት ስም እነርሱም ሆነ ደጋፊዎቻቸው ሊንቀሳቀሱ ፈጽሞ አይችሉም። በአዲስ አበባ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ለብርቱካን ሚዴቅሳ ያስተላለፉት መልዕክትና አቋም እንዲሁም የቅንጅት የፓርላማ አባሎች ያወጡት መግለጫ የሚገልጸው የዚሁ እውነት መውጣት ነጸብራቅ ነው። እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል ይሏል ይህ ነው። እውነቱ ከኢንጂር ኃይሉ ሻውል ጋር ነው። ያለማወላወል ድጋፋችንን እንስጥ። የአንድነት ኃይሉን ክፍልም እናጠናክር። ከዚህ ውጭ ግን ገለልተኛ መሆን ማለት ወያኔን መደገፍ ነው። ሊታሰብበት ይገባል።

ቅንጅት አንድ ነው !
ኢትዮጵያም አንድ ናት !
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!

መጋቢት 14 ቀን 2000 ዓ.ም